# መግቢያ

የሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት የተገልጋዩን ሕብረተሰብ የአገልግሎት ፍላጐት ለማርካትና ዓለም ከደረሰበት የአገልግሎት አሰጣጥ ደረጃ ለማድረስ የአሰራር ሥርዓቱን ለማዘመን ፣የሰው ኃይሉን የመፈፀም አቅሙን ለማጐልበት ጥረት እያደረገ ይገኛል። ከዚህ ጥረት አንዱ ሰነድ የማረጋገጥና የመመዝገብ ሥርዓትን ወቅቱ ከሚጠብቀው ሁኔታ ጋር እያሻሻሉና ዘመናዊ እያደረጉ መሄድን ያካትታል። በዚሁ መሠረት፣ የአገልግሎት ማንዋሉን ለማሻሻል በስድስት ዙር ለ560 ጉዳዩ ለሚመለከታቸው የጽ/ቤቱ ኃላፊዎች፣ ኦፊሰሮችና አረጋጋጮች እንዲሁም ከሁሉም ክልል ሰነድ የማረጋገጥና የመመዝገብ ሥራ ላይ የተሰማሩ ባለሙያዎችን በማሳተፍ ውይይትና ግብረ መልስ ለማግኘት ጥረት ተደርጓል። ሰነድ የማረጋገጥና የመመዝገብ ሥርዓቱም ሃገራዊ ይዘት እንዲኖረው ለማድረግና በፌደራልና በክልሎች የሚረጋገጡና የሚመዘገቡ ሰነዶች እኩል ተቀባይነት እንዲኖራቸው ጽ/ቤቱ ባዘጋጀው ሥልጠና ግንዛቤ እንዲያዝ የበኩሉን ድርሻ ተወጥቷል። ከዚህ በተጨማሪ በጽ/ቤቱ የሚገኙ ሁሉም ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ወጥነት ያለው አሠራር ለመፍጠር ማንዋሉን መከለስ አስፈልጓል። ለነባርና አዳዲስ የአገልግሎት ፍላጐቶችም ጭምር የአገልግሎት ቅድመ ሁኔታዎችን ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በማወያየት የማካተትና የማጥራት ሥራ በማከናወን ማንዋሉን ለማሻሻል በተቋቋመው ኮሚቴ በኩል ጥረት ተደርጓል። ረቂቅ ማንዋሉ ከ ተዘጋጀ በኋላ ተጨማሪ ግብዓት የሚሰጥበት የጋራ መድረኮችን በማዘጋጀት ማስተካከያና ግብዓት ተገኝቷል። የተገልጋዩ ሕብረተሰብ የአገልግሎት ፍላጐትና እርካታ እምርታ በማምጣት ፈጣንና ውጤታማ አገልግሎት ለመስጠትም ማንዋሉን በተከታታይነት ማሻሻል አስፈላጊ መሆኑ ታምኖበታል። ከዚህ በተጨማሪ የጽ/ቤቱን አሰራር እምነት የሚጣልበት እና ለፍርድ ቤት ክርክሮች ተጋላጭ እንዳይሆን ግልጽነትና ወጥነት ያለው አሰራርን ከመፍጠር አንፃር ማንዋሉ ትልቅ ድርሻ ይኖረዋል። በአጠቃላይ የዜጐች ወይም የተገልጋዮች ሕገ-መንግሥታዊ መብት የሆነውን ንብረት የማፍራት የመሸጥ፣የማውረስ ወይም በሌላ መንገድ የመጠቀም መብታቸውን እውን ለማድረግ ማንዋሉ አጋዥ የማስፈፀሚያ መሳሪያ ሆኖ ያገለግላል። ጽ/ቤቱም በአዋጅ ቁጥር 334/1995 እንዲሁም በማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 467/1997 የተሰጠውን ስልጣንና ሃላፊነት ለመወጣት እንዲሁም የፍትህ ሥርዓቱን ለማጐልበትና ኢንቨስትመንቱን ለማሳለጥ ይህ ሰነድ የማረጋገጥና የመመዝገብ ዝርዝር የአፈፃፀም ማንዋል በወጥነት እንዲያገለግል ታሳቢ በማድረግ በጽ/ቤቱ የሚሰጡ አገልግሎቶች ከተገልጋዩ ሕብረተሰብ ወይም ዜጐች ሊያሟሉ የሚገባቸውን የአገልግሎት ቅድመ ሁኔታ በማካተት ከ---------ጀምሮ በጽ/ቤቱ ፕሮሰስ ካውንስል ፀድቆ ተግባራዊ ሆኗል።

# ክፍል አንድ

## በጽ/ቤቱ የሚሰጡ አገልግሎቶችና የአገልግሎት ቅድመ ሁኔታዎች

## 1. ውክልና ስልጣን መስጫ ሰነድ

- ውክልና ሰጪዎች እኛ ባልና ሚስት ብለው በጽ/ቤታችን ቀርበው ውክልና ከሰጡ ተወካይ በውክልናው መሰረት አገልግሎት ፈልጐ ሲመጣ በድጋሚ ዋና የጋብቻ ማስረጃ መጠየቅ ሳያስፈልግ መስተናገድ አለባቸው፡፡
- በውጭ አገር ባሉ የኢትዮጵያ ኤንባሲ በሚሰጡ የውክልና ስልጣን ማስረጃዎች የተጠቀሰ የባል ወይም ሚስት ውክልና ወይም ለባለቤቱ ተብሎ በተፃፈ ሰነድ ዳግም የጋብቻ ማስረጃ አይጠይቅም፣
- በፍርድ ቤት የተሾመ ሞግዚት ለሆነለት ልጅ ለሌላ ሶስተኛ ወገን ንብረት ማስተዳደርን በተመለከተ ውክልና መስጠት ይችላል፡፡
- በፍ/ቤት የተሾመ ከእናት ወይም ከአባት ውጪ ሞግዚት ከሆነ በፍርድ ያገኘው መብት በመሆኑ ንብረትን ማስተዳደር በተመለከተ 3ኛ ወገን ለመወከል ቢፈልግ ተጨማሪ ስልጣን ለዚህ አላማ ፍ/ቤት ሲጠይቅና ይህንኑ ሲያቀርብ ውክልና መስጠት ይችላል
- የውክልና ሰነድ Formate ሊይዛቸው ስለሚገቡ ፍሬ ነገሮች

### 1.1 ጠቅላላ ውክልና /በፍ/ህግ ቁጥር 2203 መሠረት/

- በህግ አግባብ የተዘጋጀ የውክልና ስልጣን መስጫ ሰነድ
- የወካይ/የወካዮች/ መታወቂያ
- ኩባንያ ከሆነ የመመስረቻ ጽሁፍ ፣መተዳደሪያ ደንብ እና ቃለ ጉባኤ፣የታደሰ የንግድ ዋና ምዝገባ

### 1.2 የአስተዳደር ስራ በፍ/ህግ ቁጥር 2204 መሰረት

- የወካይ ሀብት የማስቀመጥ፣ የመጠበቅ፣ ከ3 ዓመት ለማያልፍ ዘመን የማከራየት፣ በብድር የተሰጠውን ሀብት የመሰብሰብ፣ ከሀብቱ የሚመጣውን

ገቢ ተቀብሎ የማስቀመጥና ለተከፈሉ እዳዎች ደረሰኝ የመስጠት ስራዎች ሁሉ እንደ አስተዳደራዊ ተግባር ይቆጠራሉ፡፡

- በህግ አግባብ የተዘጋጀ የውክልና ስልጣን መስጫ ሰነድ
- የወካይ/የወካዮች/ መታወቂያ

## 1.3 ልዩ ውክልና /በፍ/ህግ ቁጥር 2205 መሠረት/

- በህግ አግባብ የተዘጋጀ የውክልና ስልጣን መስጫ ሰነድ
- የወካይ/የወካዮች/ መታወቂያ
- በውክልናው ላይ የተጠቀሰውን ንብረት ለመወከል የግድ ለሶስተኛ ወገን ለማስተላለፍ የሚያስችል አግባብነት ያለው የባለቤትነት ማስረጃ
- ተወካይ 3ኛ ወገን ለመወከል ያልተፈቀደለት ቢሆንም በፍ/ሕ/ቁጥር 2215/3 መሰረት ተገቢውን ምክንያት ገልፆ ያስተዳደር ስራን ብቻ ሊወክል ይችላል
- በፊርማ ናሙና ብቻ የሚሰጡ ውክልናዎች በመጀመሪያ በሚሰጡበት ሰዓት ወካዩች ከውል ወይም ከህግ የመነጨ ስልጣን ያላቸው ለመሆኑ እንዲሁም በውክልና ውስጥ የሚጠቀሱ ነገሮች ማስረጃ የሚፈልጉ ሆነው ሲገኙ ይኸው ማስረጃ ያላቸው መሆኑ ተጣርቶ ሊሰጥ ይገባል፡፡

## 1.4 የቤተሰብ ውክልና /በፍ/ R / R ህግ ቁጥር 58 መሠረት/

- በህግ አግባብ የተዘጋጀ የውክልና ስልጣን መስጫ ሰነድ
- የወካይ/የወካዮች/ መታወቂያ
- የስጋ ዝምድና መኖሩን የሚያረጋግጥ ማስረጃ
- የሚወካከሉት ባልና ሚስት ከሆኑ የጋብቻ ማስረጃ

## 1.5 የጠበቃ ውክልና /በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 63 መሠረት/

በየትኛውም ውል ለማዋዋል ስልጣን በተሰጠው አካል የተሰጠ የውክልና ስልጣን በየትኛውም የጽ/ቤቱ ቅርንጫፎች መሻር ይቻላል፡፡

- በጠበቃ ውክልና ላይ የፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 63ን በመጥቀስ እንዲሁም በፍ/ሕ/ቁጥር 2204 መሰረት የጉዳይ ማስፈፀም ውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡
- በህግ አግባብ የተዘጋጀ የውክልና ስልጣን መስጫ ሰነድ

- የወካይ/የወካዮች/ መታወቂያ
- በጽ/ቤቱ የተመዘገበ፣ በእዳና እገዳ የተጣራና የታደሰ የጥብቅና ፈቃድ

## 2. የውክልና ሥልጣን መሻሪያ/በፍ/ህግ ቁጥር 2226/1/ መሠረት/

- በህግ አግባብ የተዘጋጀ የውክልና ስልጣን መሻሪያ ሰነድ
- የሻሪ ወይም የሻሪዎች የታደሰ መታወቂያ
- ቀደም ሲል የተሰጠ ዋና የውክልና ሥልጣን ሰነድ

## 2.1 የውክልና ሥልጣን ስለመተው/በፍ/ህግ ቁጥር 2229/1/ መሠረት/

- በህግ አግባብ የተዘጋጀ የውክልና ስልጣን መተው ሰነድ
- የወኪሉንወይም የወኪሎቹን የታደሰ መታወቂያ
- ወኪሉ ከወካዩ ቀደም ሲል የተሰጠውን ዋና የውክልና ሥልጣን ሰነድ

## 3. በግልጽ የሚደረግ ኑዛዜ/በፍ/ህግ ቁጥር/ 891 መሠረት

- በህግ አግባብ የተዘጋጀ የኑዛዜ ሰነድ (ግልጽ ወይም በተናዛዡ) የተደረገ ኑዛዜ
- ሁለት ምስክሮች
- የተናዛዥ እና የምስክሮች የታደሰ መታወቂያ

## 4. የኑዛዜ መሻሪያ በፍ/ብ/ህግ/ቁጥር898

- በህግ አግባብ የተዘጋጀ የኑዛዜ መሻሪያ ሰነድ (ግልጽ ወይም በተናዛዡ) የተደረገ ኑዛዜ
- ሁለት ምስክሮች
- የኑዛዜ ሻሪውና የምስክሮች የታደሰ መታወቂያ
- በጽ/ቤቱ የተመዘገበው የኑዛዜ ሰነድ

## 5. የተተረጎሙ ሰነዶችን ማረጋገጥ በዓዋጅ 334/95 አንቀጽ 3 መሠረት

- የትርጉም ቤቱ በቃለ መሃላ የተደገፈ ደብዳቤ
- በጽ/ቤቱ የተመዘገበና በእዳና እገዳ የተረጋገጠ የተርጓሚው የፊርማ ናሙና
- ከመተርጐሙ በፊት ያለው ዋና ሰነድ
- በሚፈለገው ቋንቋ ተዘጋጅቶ የቀረበው ሰነድ ዋናውና ሁለት ኮፒ

## 6. በሌሎች ሠነድ የማረጋገጥ ሥልጣን በተሠጣቸው አካላት ተረጋግጠው የሚቀርቡ ሰነዶች በአዋጅ 334/95 አንቀጽ 26 መሠረት

### 6.1 በውጭ ጉዳይ ተረጋግጠው የቀረቡ ሰነዶችን መመዝገብ

- ከውጭ ጉዳይ ሚ/ር ተረጋግጠው ለሚቀርቡ ሰነዶች ባለጉዳዩ ሰነዱን ለማስመዝገብ ጽ/ቤቱ ዘንድ ይዞ ሲቀርብ የተከፈለበት ደረሰኝ እንዲያቀርብ ወይም እንዲያሳይ አይገደድም
- በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ ባንኮችና መሰል ተቋማት ከውጭ ሀገራት የሚመጡ የውክልናና መሰል ሰነዶችን ስለትክክለኛነታቸው ማረጋገጫ ሲጠይቁ ሰነዱ የውጭ ጉዳይ የፊርማ ናሙና መሆኑ ከማረጋገጥ ውጪ በጽ/ቤቱ ፊት ያልተፈረመና ያልመረመረው መሆኑን ገልፆ መልስ መስጠት
- በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ተረጋግጦ የሚቀርብ ሰነድ፡-
  - የአረጋጋጭ ሙሉ ስምና የስራ ኃላፊነት ፊርማ መኖሩን ማረጋገጥ
  - የአረጋጋጩ ቲተርና ማህተም ያረፈበት ዋና ሰነድና ኮፒ መኖሩን ማረጋገጥ
- በጽ/ቤቱ የተመዘገበና በእዳና እገዳ የተጣራ የፊርማ ናሙና

### 6.2 በመከላከያ ሠራዊት የክፍል ሹሞች ተረጋግጠው የቀረቡ ሰነዶችን መመዝገብ

- በመከላከያ ሠራዊት የክፍል ሹሞች የተረጋገጠ፣ስልጣን ባለው አካል የተፈረመ የስም ቲተርና ማህተም ያረፈበት ዋና ሰነድ እና ኮፒ
- በጽ/ቤቱ የተመዘገበና በእዳና እገዳ የተጣራ የፊርማ ናሙና

### 6.3 በፌዴራል ማረሚያ ቤቶች ተረጋግጠው የቀረቡ ሰነዶችን መመዝገብ

- በአዋጅ ቁጥር 334/95 መሰረት የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች የታራሚዎችን ሰነድ የማረጋገጥ ስልጣን ያለው ስለሆነ በተቋሙ በአድራሻ የቀረቡለትን ሰነዶች አረጋግጦ ሲልክ ጽ/ቤቱ የመመዝገብ ተግባር ያከናውናል።
  - በፌዴራል ማረሚያ ቤቶች የሥራ ኃላፊዎች (ሹሞች) የተረጋገጠ፣ስልጣን ባለው አካል የተፈረመ የስም ቲተርና ማህተም ያረፈበት ዋና ሰነድ እና ኮፒ፣
  - በጽ/ቤቱ የተመዘገበና በእዳና እገዳ የተጣራ የፊርማ ናሙና።

## 7. የሰነድ ቅጂዎችን ከዋናው ጋር ማመሣከር በዓዋጅ ቁ/ 334/95 አንቀጽ 12መሠረት

- እስቱደንት ኮፒ፣ ሊብሬ፣ የቤት ካርታ፣ የጋብቻ ወይም ያላገባ ማስረጃዎች፣ የልደት ሰርተፍኬት ኮፒ ማመሳከሪያ አይሰራላቸውም።
- ከግል ተቋማት የሚመጡ የት/ማስረጃዎችን በተመለከተ ኮፒ ከኦርጅናሉ ጋር ይመሳከርልኝ ጥያቄ ሲቀርብ የት/ማስረጃው ጀርባ ላይ የት/ሚር ማህተም ወይም ተቋሙ እውቅና ስለመኖሩ ከሚመለተው አካል ደብዳቤ ማምጣት ያስፈልጋል።
  - ከህጋዊ ተቋም የተሰጠ ዋና ሰነድ እንዲሁም የሰነዱ ኮፒ፣

## 8. ቃለ መሃላ ሰነድ /በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 92/205/ መሠረት/

- በህግ አግባብ የተዘጋጀ የቃለ መሃላ ማመልከቻ
- የታደሰ መታወቂያ፣
- በቃለ መሀላ ሰነድ ውስጥ ማስረጃ የሚጠይቁ ነገሮች ከተጠቀሱ አግባብነት ያላቸው ማስረጃዎች ሊቀርቡ ይገባል።

## 9. ማረጋገጫ/ ዲክላሬሽን

- በህግ አግባብ የተዘጋጀ የቃለ መሃላ ማመልከቻ
- የታደሰ መታወቂያ፣
- በዲክላራሲዩን ላይ ስለተጠቀሰው ጉዳይ ህጋዊ ማስረጃ ለምሳሌ ዋናው የልደት የምስክር ወረቀት፣የሕክምና ማስረጃ...፣
- በዲክላራሲዩን ሰጪውና በተቀባዩ መካካል የሥጋ ዝምድና ወይም የህግ መሰረት መኖሩን ማረጋገጥ

# 10 ግዙፍነት ያላቸውና የሌላቸው ንብረቶች በውል ስለ ማስተላለፍ

## 10.1የተንቀሳቃሽ ንብረት ልዩ ልዩ ውሎች በፍ/ብ/ህ/ቁጥር 2266 መሠረት

### 10.1.1 የመኪና ሽያጭ ውል ኮድ 1 ፣3፣2

- በህግ አግባብ የተዘጋጀ የሽያጭ ውል ሰነድ/ፎርም/
- እዳና እገዳ ስላለመኖሩ ከዕዳና እገዳ ክፍል የቀረበ ማረጋገጫ፣
- የባለቤትነት መታወቂያ ሊብሬ፣

- የሻጭና የገዥ የታደሰ መታወቂያ፣
- ሻጭ/ገዢ ተወካይ ከሆነ የውክልና ሥልጣን፣
- ንብረቱ የንግድ ማህበር ከሆነ ከህግ ወይም ከውል የመነጨ ስልጣን፣
- የሻጭ ያላገባ ወይምያገባ ማስረጃ /የፈቃድ ስምምነት/፣
- ከትራንስፖርት ባለስልጣን የሚሰጥ የመኪና ዋጋ ግምት እና ክሊራንስ፣
- ከገቢዎችና ጉምሩክ የሚሰጥ ክሊራንስ ለኮድ 1 እና 3 ብቻ፣
- ለኮድ 1 እና 3 ብቻ 10 ዓመት ቢሞላውም ከቀረጥ ነፃ ከሆነ ከገቢዎችና ጉምሩክ ከቀረጥ ነፃ መብት ማስተላለፍ ባለሥልጣን የተፃፈ ደብዳቤ፣
    - የመጫን አቅማቸው ከ45 ሰው በላይ የሆኑ የህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎችና ከ100 ኩንታል በላይ የመጫን አቅም ያላቸው የጭነት ተሽከርካሪዎች ከቀረጥ ነፃ የገቡ ቢሆኑም ካለ ቀረጥ ነጻ መብት ፈቃድ ሰጪ ባለሥልጣን እውቅና ሳያስፈልግ በሽያጭ ሊተላለፉ ይችላሉ።

### 10.1.2 የመኪና ሽያጭ ውል ኮድ 5፣11፣8 እና ሌሎች ለመሳሰሉት

- ከቀረጥ ነፃ መብት የገቡ ተሽከርካሪዎች ከባለሥልጣኑ እውቅናና ፈቃድ ውጭ በውክልና ሆነ በስጦታ መተላለፍ አይችሉም።

- በህግ አግባብ የተዘጋጀ የሽያጭ ውል ሰነድ/ፎርም/፣
- እዳና እገዳ ስላለመኖሩ በተቋሙ መረጋገጡን ማጣራት /ኮድ 5,11,8......መሆን እግድ ነው/፣
- የባለቤትነት መታወቂያ ሊብሬ፣
- የሻጭና የገዥ የታደሰ መታወቂያ፣
- ሻጭ ተወካይ ከሆነ የውክልና ሥልጣን፣
- የሻጭ ከህግ ወይም ከውል የመነጨ ስልጣን
- ከትራንስፖርት ባለስልጣን የሚሰጥ የመኪና ዋጋ ግምት
- ከፌዴራል ጉዳዩች ሚ/ር የማስተላለፍ እውቅና ደብዳቤ ለኮድ /5፣35፣ 8 እና ለመሳሰሉት ብቻ/፣

### 10.1.3 የመኪና ስጦታ ውል ስምምነት

- በህግ አግባብ የተዘጋጀ የስጦታ ውል ሰነድ/ፎርም/፣
- እዳና እገዳ ስላለመኖሩ በተቋሙ መረጋገጡን ማጣራት፣
- የባለቤትነት መታወቂያ ሊብሬ፣
- የስጦታ አድራጊው፣የስጦታ ተቀባይ እና የሁለት ምስክሮች የታደሰ መታወቂያ፣
- ስጦታ አድራጊው ተወካይ ከሆነ በህግ አግባብ የተሰጠ የውክልና ሥልጣን
- የስጦታ አድራጊው ያላገባ ወይምያገባ ማስረጃ /የፈቃድ ስምምነት /ያላገባ ከሆነ ማስረጃው 6 ወር ያለፈበት መሆን የለበትም/
- ከትራንስፖርት ባለስልጣን የሚሰጥ የዋጋ ግምት እና ክሊራንስ/ለኮድ 1 እና 3/፣
- ከገቢዎችና ጉምሩክ የሚሰጥ ክሊራንስ /ለኮድ 1 እና 3/፣

### 10.1.4 የመኪና ድርሻ ስጦታ/ድርሻ ሽያጭ ለማድረግ ለሚመጡ ባለጉዳዩች

- ንብረቱ በውስጥ የመጣ ከሆነ ስም ባይዞርም የውርስ አጣሪ ሪፖርት፣
- ከመንገድና ትራንስፖርት ባለስልጣን የተሰጠ የመኪና ግምት፣
- በህግ አግባብ የተዘጋጀ ውል፣
- ለኮድ 1 እና 3 የገቢዎች እና የመንገድ ት/ር ክሊራንስ፣
- ከውርስ ውጭ ከሆነ ደግሞ ከላይ በ10.1.2 እና በ10.1.3 የተጠቀሱት መስፈርቶች እንደአግባብነታቸው ተፈፃሚ ይሆናሉ።

### 10.1.5 የኮንስትራክሽን ማሽነሪ ሽያጭ ወይም ስጦታ ውል

- በህግ አግባብ የተዘጋጀ የውል ሰነድ፣
- እዳና እገዳ ስላለመኖሩ በተቋሙ መረጋገጡን ማጣራት፣
- ከከተማ ልማት እና ኮንስትራክሽን ሚ/ር የተሰጠ ሊብሬ፣ግምት ፎርም እና ክሊራንስ፣
- የገቢዎች ጉምሩክ ግምት እንዲሁም የሻጭና የገዥ ግምት የስራና ከተማ ልማት ሚ/ር ግምት ቢቀርብ ሊወሰድ የሚገባው ትልቁ ግምት ነው
- ከገቢዎችና ጉምሩክ ክሊራንስ፣
- ከቀረጥ ነፃ የገባ ከሆነ ከገቢዎችና ጉምሩክ ከቀረጥ ነፃ መብት ላላቸው የማስተላለፍ መብት ደብዳቤ፣
- የሻጭ፣ የገዥ እና የሁለት ምስክሮች የታደሰ መታወቂያ፣
- ንብረቱ የንግድ ማህበር ከሆነ የሻጭ ከህግ ወይም ከውል የመነጨ ስልጣን፣

- ሻጭ እና /ወይም ስጦታ ተቀባይ ተወካይ ከሆነ በህግ አግባብ የተሰጠ የውክልና ሥልጣን፣
- የሻጭ 6 ወር ያላለፈበት ያላገባ ወይም ያገባ ማስረጃ /የፈቃድ ስምምነት፣/
- የገቢዎች የግብር አከፋፈል ክሊራንስ።

### 10.1.6 የተሽከርካሪ ሞተር ሽያጭ ወይም ስጦታ ውል

- በህግ አግባብ የተዘጋጀ የውል ሰነድ፣
- እዳና እገዳ ስላለመኖሩ በተቋሙ መረጋገጡን ማጣራት፣
- ከትራንስፖርት ባለሥልጣን የዋጋ ግምትና ደብዳቤ፣
- ሁለት የሰው ምስክሮች፣
- የሻጭ/ስጦታ አድራጊ፣ የገዢ/ስጦታ ተቀባይ እና የምስክሮች የታደሰ መታወቂያ፣
- ከቀረጥ ነፃ የገባ ከሆነ ከገቢዎችና ጉምሩክ ከቀረጥ ነፃ መብት ክሊራንስ፣
- ሻጭ ወይም ስጦታ አድራጊው ተወካይ ከሆነ በህግ አግባብ የተሰጠ የውክልና ሥልጣን፣
- የሻጭ 6 ወር ያላለፈበት ያላገባ ወይም ያገባ ማስረጃ /የፈቃድ ስምምነት፣
- የሻጭ የባለቤትነት ማረጋገጫ ሊብሬ።

### 10.1.7 የተለያዩ ተንቀሳቃሽ ማሽነሪዎች ሽያጭ ወይም ስጦታ

- በህግ አግባብ የተዘጋጀ ውል፣
- ከእዳና እገዳ ነፃ መሆኑ፣
- የተዋዋዩች መታወቂያ የታደሰ፣
- የሻጭ የጋብቻ ማስረጃ/ያላገባ ከሆነ 6 ወር ያልሞላው፣
- ማሽነሪው የገባበት ዲክላራሲዩን፣
- የታደሰ ንግድ ስራ ፈቃድ እና ዋና ምዝገባ ይህ ከሌለ አለመኖሩን የሚገልጽ የንግድ ሚ/ር ደብዳቤ፣
- ከቀረጥ ነፃ ከሆነ የቀረጥ ነፃ ዝውውር ደብዳቤ፣
- የገቢዎች ጉምሩክ ክሊራንስ፣
- የሁለት ምስክሮች የታደሰ መታወቂያ፣

### 10.1.8 የተንቀሳቃሽ ንብረት ኪራይ ውል ስምምነት

- በህግ አግባብ የተዘጋጀ የውል ሰነድ፣
- የአከራይ፣የተከራይ፣ የሁለት ምስክሮች የታደሰ መታወቂያ፣
- አከራይ ወይም ተከራይ ተወካይ ከሆነ በህግ አግባብ የተሰጠ የውክልና ሥልጣን፣
- የአከራይ ያላገባ ወይምያገባ ማስረጃና /የፈቃድ ስምምነት/፣
- የአከራይ 6 ወር ያላለፈበት የባለቤትነት ማረጋገጫ ማስረጃ፣
- ንብረቱ የንግድ ማህበር ከሆነ ከህግ ወይም ከውል የመነጨ ስልጣን ሰነድ፣
- የንግድ ሥራ ፈቃድ የታደሰ፣ የንግድ ዋና ምዝገባ ሰርተፍኬት የታደሰ።

### 10.1.9. የመኪና የድርሻ መልቀቅ ውል ስምምነት ኮድ 1 ፣ 2፣ 3

- በህግ አግባብ የተዘጋጀ የውል ሰነድ፣
- እዳና እገዳ ስላለመኖሩ በተቋሙ መረጋገጡን ማጣራት፣
- የግራ ቀኝ ተዋዋዬችና የሁለት ምስክሮች የታደሰ መታወቂያ፣
- የግራ ቀኝ ተዋዋዬች ና ተወካይ ከሆነ በህግ አግባብ የተሰጠ የውክልና ሥልጣን፣
- መኪና/የሞተር ሳይክል ከሆነ የባለቤትነት ማረጋገጫ ሊብሬ፣
- የፍርድ ቤት የወራሽነት ማስረጃ።

## 10.2 የማይንቀሳቀሱ ንብረቶች ልዩ ልዩ ውሎች በፍ/ብ/ህ/ቁጥር 1723 እና 2875 መሠረት

- በስጦታ፣ በውርስ፣በሽያጭ ወይም በሌላ መንገድ ተገልጋዮች ንብረት ለማስተላለፍ ሲመጡ ካርታው ከጀርባው ከተረጋገጠና የወራሾች ዝርዝር ከጀርባው ከተፃፈ ወደ ኋላ ሄዶ ሌሎችን የወራሽነት ማስረጃዎች ማየት ሳያስፈልግ መስተናገድ አለባቸው።
- በውርስ ወይም በስጦታ ለተገኘ ንብረት የጋብቻ ማስረጃ አይጠየቅም
- ለሽያጭ ወይም ለኪራይ የቀረቡ የማይንቀሳቀሱ ንብረቶች ከአዲስ አበባ አስተዳደር ውጭ በጽ/ቤቱ አይስተናገዱም።
- ከጋብቻ በፊት በጽ/ቤታችን ቀርበው ንብረት ያስመዘገቡ ተጋቢዎች ንብረታቸውን ለማስተላለፍ ሲመጡ የተጋቢዎቹ ስምምነት አያስፈልግም።
- ለአካለ መጠን ያልደረሱ ልጆችን በተመለከተ ንብረት ለመግዛት ና ለመሸጥ ሁለቱም ወላጆች ሊገኙ ይገባል ወይም በውክልና ሥልጣን ከሆነ መስተናገድ ይቻላል። ሆኖም

የህፃኑ ንብረት በውርስ የመጣ ከሆነ ሞግዚቱ ማንም ቢሆን ንብረቱን ለመሸጥ ተጨማሪ ስልጣን በፍ/ቤት ሊሰጠው ይገባል።

- በፍርድ ቤት የተሾመ ሞግዚት እናት ወይም አባት ከሆኑ በልጁ ስም የተመዘገበ የማይንቀሳቀስ ንብረትን መሸጥ መለወጥ ማከራት ይችላል።
- በፍርድ ቤት ውሳኔ የተላለፈ ንብረት ስም ሳይዞር ማከራየት አይቻልም። ሆኖም ከፍርድ ቤት ወራሽነት በተጨማሪ ከሚመለከተው አካል ስም ለማዞር በሂደት ላይ መሆኑንና ቢያከራዩ አንቃወምም የሚል ደብዳቤ ከአዲስ አበባ አስተደደር የሚመለከታቸው አካላት ሲያቀርቡና ሁሉም ወራሾች ከቀረቡ እሰከ አንድ ዓመት ብቻ ደብዳቤው ከተጻፈበት ቀን ጀምሮ የሚታሰብ መስተናገድ ይችላሉ።

## 10.2.1 የመኖሪያ ቤት ሽያጭ ወይም ስጦታ ውል

- በህግ አግባብ የተዘጋጀ የውል ሰነድ፣
- እዳና እገዳ ስላለመኖሩ በተቋሙ መረጋገጡን ማጣራት፣
- እንደ አስፈላጊነቱ ግብር የተከፈለበት ደረሰኝ፣
- የግራ ቀኝ ተዋዋዬችና የሁለት ምስክሮች የታደሰ መታወቂያ፣
- ሻጭ ተወካይ ከሆነ በህግ አግባብ የተሰጠ የውክልና ሥልጣን
- የሻጭ 6 ወር ያላለፈበት ያላገባ ወይምያገባ ማስረጃ /የፈቃድ ስምምነት/
- የሻጭ የባለቤትነት ማረጋገጫ ካርታ
- ስጦታው የሚደረገው በውክልና ከሆነ ስጦታ ተቀባዩ በስም በግልጽ በውክልናው ላይ ሊጠቀስ ይገባል።

## 10.2.2 የንግድ ድርጅት ቤት ሽያጭ ወይም ስጦታ ውል

- የኮንዶሚኒየም ንግድ ቤት ሽያጭን በተመለከተ ልክ እንደሌላው የንግድ ድርጅት ቤት ሽያጭ የሚስተናገድ ይሆናል።

- በህግ አግባብ የተዘጋጀ የውል ሰነድ፣
- እዳና እገዳ ስላለመኖሩ በተቋሙ መረጋገጡን ማጣራት፣
- እንደአስፈላጊነቱ የግብር ደረሰኝ፣
- የታደሰ የንግድ ሥራ ፈቃድና የዋና ምዝገባ ሰርተፍኬት

- የሻጭ/የስጦታ አድራጊው 6 ወር ያላለፈበት ያላገባ ወይም ያገባ ማስረጃና የተጋቢዎች ፈቃደኛነት፣
- እንደአስፈላጊነቱ የታክስ አስከፋይ መ/ቤት ክሊራንስ፣
- ንብረቱ የንግድ ማህበር ከሆነ ከህግ ወይም ከውል የመነጨ ስልጣን ሰነድ፣
- ድርጅቱ ቤቱን የሚጨምር ከሆነ ካርታና፣የጋብቻ ማስረጃ ጋብቻ ከሌለ ይህንኑ የሚያረጋግጥ 6 ወር ያላለፈበት ያላገባ ማስረጃ
- ሻጭ/የስጦታ አድራጊው ወይም ገዥ/የስጦታ ተቀባዩ በውክልና ከሆነ በህግ አግባብ የተሰጠ የውክልና ሥልጣን
- የሻጭ/የስጦታ አድራጊው ፣ የገዥ/የስጦታ ተቀባዩ እና የሁለት ምስክሮች የታደሰ መታወቂያ
    - **በሚቀርበው ውል ላይ የንግድ ድርጅቱ በንግድ ሥራ ላይ ያልተሰማራ ከሆነ የግብር ደረሰኝ፣ የታክስ ክሊራንስ እንዲያቀርብ አይገደደም**
    - **የባለቤትነት ካርታ ጀርባው ስለትክክለኛነቱ በአንድ ዓመት የተረጋገጠ ማህተም**

### 10.2.3 የንግድ መደብር/መድብል ሽያጭ ወይም ስጦታ ውል

- በህግ አግባብ የተዘጋጀ የውል ሰነድ፣
- እዳና እገዳ ስላለመኖሩ በተቋሙ መረጋገጡን ማጣራት፣
- የታደሰ የንግድ ሥራ ፈቃድና የንግድ ዋና ምዝገባ ሰርተፍኬት፣
- የታክስ አስከፋይ መ/ቤት ክሊራንስ፣
- ንብረቱ የንግድ ማህበር ከሆነ ከህግ ወይም ከውል የመነጨ ስልጣን፣
- 6 ወር ያላለፈበት ያላገባ ማስረጃና ያገባ ከሆነ የጋብቻ ማስረጃና የተጋቢዎች የፈቃድ ስምምነት የሚያረጋግጥ፣
- የግራ ቀኝ ተዋዋዬች ወኪሎች ከሆኑ በህግ አግባብ የተሰጠ የውክልና ስልጣን፣
- የግራ ቀኝ ተዋዋዬች ና የሁለት ምስክሮች የታደሰ መታወቂያ።

### 10.2.4 ሀ/ የማይንቀሳቀስ ንብረት ኪራይ ውል ስምምነት በፍ/ብ/ህ/ቁጥር 2696 መሠረት

- በህግ አግባብ የተዘጋጀ የውል ሰነድ፣
- ካርታ ኮፒ፣ ውሉ በውክልና ከሆነ የውክልና ስልጣን፣ የምስክሮች የመታወቂያ ኮፒ፣
- የአከራይ ያላገባ ወይም ያገባ ማስረጃ ከፍቃድ ስምምነት ጋር፣

- ካርታው በባንክ የተያዘ ከሆነ በካንኩ አድራሻ ለጽ/ቤቱ በሺ'ኘ ድብዳቤ የሚላኩ ኪራይ ይፈቀድላቸው የኮፒ ካርታ በቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ገቢ ተደርጎ ለውስጥ አገልገሎት ለ6 ወር ብቻ ያገለግላል።
- ሰነድ አልባ ይዞታዎች ከሚመለከለተው አካል የባለቤትነት ማረጋገጫ ወይም ካርታ ሊሰጣቸው በሂደት ላይ መሆኑንና እንዲያከራዩ የሚገልጽ ደብዳቤ ተጠቅሶ ከተሰጣቸው እሰከ አንድ ዓመት ብቻ ለኪራይ መስተናገድ ይችላሉ።
- በፍርድ አፈጻጸም የተሸጠ ንብረት ከሚመለከተው አካል ስም ለማዞር በሂደት ላይ መሆኑንና ቢያከራዩ አንቃወምም የሚል ደብዳቤ ሲያቀርቡ እሰከ አንድ ዓመት ብቻ መስተናገድ ይችላሉ።

ለ/ ንብረቱ በውርስ የተገኘ እና ካርታው ወደ ወራሾች ያልዞረ ሲሆን

- የወራሽነት ማስረጃ የውርስ አጣሪ ሪፖርት /የኑዛዜ ሰነድ/ እንዲሁም
- ከግማሽ በላይ ወራሾች ከቀረቡ እሰከ 3 ዓመት ብቻ የሚደርስ የኪራይ ውል መዋዋል ይችላሉ።
- የምስክሮች መታወቂያ ኮፒ ፣ ውሉ በውክልና ከሆነ የውክልና ሰነድ

ሐ/ከግማሽ በላይ የሆኑ የንብረት ተጋሪዎች ከውርስ ውጭ አከራይ ሆነው በሚቀርቡበት ጊዜ፣

- በህግ አግባብ የተዘጋጀ የውል ሰነድ
- በስማቸው የዞረ ካርታ
- የአከራይ፣የተከራይ፣ የሁለት ምስክሮች የታደሰ መታወቂያ
- አከራይ ወይም ተከራይ ተወካይ ከሆነ የውክልና ሥልጣን
- የአከራይ ያላገባ ወይምያገባ ማስረጃና /የፈቃድ ስምምነት/

☛ በወራሽነት ማስረጃ ብቻ አይስተናገዱም

- ❖ **ንብረቱ የንግድ ማህበር ከሆነ ከህግ ወይም ከውል የመነጨ ስልጣን፣ የታደሰ የንግድ ሥራ ፈቃድና፣ የንግድ ዋና ምዝገባ ሰርተፍኬት፣**
- ❖ **ንብረቱ ለትርፍ ያልተቋቋመ ማህበር ከሆነ ከበጎ እድራጎት ማህበራት ኤጀንሲ የማከራየት ፈቃድ ደብዳቤ ማቀረብ አለበት፣**
- ❖ **አንድን ህንጻ በተለያየ መንገድ ሊተላለፍ ሆነ ለኪራይ ሲቀርብ በውሉ ሰነድ ላይ ህንጻው በህንጻ መጠቀሚያ ፈቃድ መመሪያ የማይሸፈን መሆኑን መገለጽ አለበት**

## 10.2.5. የማይንቀሳቀስ ንብረት የድርሻ ስጦታ ወይም ሽያጭ ውል ስምምነት በፍ/ብ/ህ/ቁጥር 1260 እና 1262 መሠረት

- በህግ አግባብ የተዘጋጀ የውል ሰነድ፣
- እዳና እገዳ ስላለመኖሩ በተቋሙ መረጋገጡን ማጣራት፣
- የንግድ ከሆነ ከገቢዎችና ጉምሩክ የተሰጠ ክሊራንስ፣ የታደሰ ዋና ምዝገባና ንግድ ፈቃድ
- የግራ ቀኝ ተዋዋዬችና የሁለት ምስክሮች የታደሰ መታወቂያ
- የግራ ቀኝ ተዋዋዬች ተወካይ ከሆነ በህግ አግባብ የተሰጠ የውክልና ሥልጣን
- የንግድ ድርጅት ከሆነ ከሕግ ወይም ከውል የመነጨ ሥልጣን፣
- የንግድ መደብር ከሆነ የታደሰ ንግድ ፈቃድ እና ዋና ምዝገባ፣
- 6 ወር ያላለፈበት ያላገባ ማስረጃ ወይም ጋብቻ ካለ የጋብቻ ማስረጃና የተጋቢዎች ስምምነት።
  - ❖ **የባለቤትነት ካርታ ጀርባው ስለትክክለኛነቱ በአንድ ዓመት ውስጥ የተረጋገጠ ማህተም**
  - ❖ **ንብረቱ ለትርፍ ያልተቋቋመ ማህበር ከሆነ ከበጎ እድራጎትና ማህበራት ኤጀንሲ የማከራየት ፈቃድ ድብዳቤ ማቀረብ አለበት።**

## 10.2.6 የኮንዶሚኒየም ቤት ሽያጭ ውል ስምምነት

- በህግ አግባብ የተዘጋጀ የውል ሰነድ፣
- እዳና እገዳ ስላለመኖሩ በተቋሙ መረጋገጡን ማጣራት፣
- የባለቤትነት ካርታ ጀርባው ስለትክክለኛነቱ የተረጋገጠ ማህተም

- የኮንዶሚኒየሙ ባለቤት ቤቱን ከተረከበው አምስት አመት ስለመሙላቱ ከሚመለከተው አካል የቀረበ የሰነድ ማረጋገጫ፣
- የግራ ቀኝ ተዋዋዬችና የሁለት ምስክሮች የታደሰ መታወቂያ
- የግራ ቀኝ ተዋዋዬች ተወካይ ከሆነ በህግ አግባብ የተሰጠ የውክልና ሥልጣን
- የሻጭ ያላገባ ወይም 6 ወር ያላለፈበት ጋብቻ ካለ የጋብቻ ማስረጃና የተጋቢዎች ስምምነት፣
    - **የባለቤትነት ካርታ ጀርባው ስለትክክለኛነቱ የተረጋገጠ ማህተም**

## 10.2.7. የማህበራት ቤት ሽያጭ ውል ስምምነት

- በህግ አግባብ የተዘጋጀ የውል ሰነድ፣
- እዳና እገዳ ስላለመኖሩ በተቋሙ መረጋገጡን ማጣራት፣
- የባለቤትነት ካርታ ጀርባው ስለትክክለኛነቱ የተረጋገጠ ማህተም፣
- ከክፍለ ከተማ ማህበራት ማደራጃና ከተደራጀው ማህበር ዕዳ እንደሌለበት የማረጋገጫ ደብዳቤ፣
- የሻጭ ጋብቻ 6 ወር ያላለፈበት ያላገባ ማስረጃ ወይም ጋብቻ ካለ የተጋቢዎች ስምምነት፣
- የግራ ቀኝ ተዋዋዬችና የሁለት ምስክሮች የታደሰ መታወቂያ፣
- የግራ ቀኝ ተዋዋዬች ተወካይ ከሆነ በህግ አግባብ የተሰጠ የውክልና ሥልጣን፣
- በግብር ደረሰኝ ኮፒ ላይ የክፍለ ከተማ ማህተም፣

## 10.2. 8. የሊዝ መብት ማስተላለፍ ውል ስምምነት

- በህግ አግባብ የተዘጋጀ የውል ሰነድ፣
- እዳና እገዳ ስላለመኖሩ በተቋሙ መረጋገጡን ማጣራት፣
- የባለቤትነት ካርታ ጀርባው ስለትክክለኛነቱ በአንድ ዓመት ውስጥ የተረጋገጠ ማህተም፣
- ከሚመለከተው አካል የሊዝ ውል ስምምነት፣
- የቅድሚያ ክፍያ ደረሰኞች ወይም ክፍያው ከተጠናቀቀ የግብር ደረሰኝ፣

- የሻጭ 6 ወር ያላለፈበት ያላገባ ማስረጃ ወይም ጋብቻ ካለ የጋብቻ ማስረጃና የተጋቢዎች ስምምነት፣
- የግራ ቀኝ ተዋዋዬች የሁለት ምስክሮች የታደሰ መታወቂያ
- ሻጭና/ወይም ገዢ ተወካይ ከሆነ በህግ አግባብ የተሰጠ የውክልና ሥልጣን፣
- የሚተላለፈው የሊዝ መብት የድርጅት ከሆነ ከገቢዎች ክሊራንስ።

## 10.2.9. የድርሻ መልቀቅ ውል ስምምነት በፍ/ብ/ህ/ቁጥር1262

- በህግ አግባብ የተዘጋጀ የውል ሰነድ፣
- የድርሻ ለቃቂ፣ የተቀባይና የሁለት ምስክሮች የታደሰ መታወቂያ፣
- ድርሻ ለቃቂ ወይም ተቀባይ ተወካይ ከሆነ በህግ አግባብ የተሰጠ የውክልና ሥልጣን፣
- የፍርድ ቤት የወራሽነት ወይም የባለቤትነት ማስረጃ፣
- ባል ለሚስት ወይም ልጆች በሂወት ላሉ ወላጆች ድርሻ መልቀቅ አይችሉም። ነገር ግን በውርስ የተገኘውን ይህንን ንብረት በድርሻ ስጦታ ወይም ሽያጭ በሂወት ላሉ ወላጆች ማስተላለፍ ይችላሉ።
- የውርሱ ንብረት የአክሲዮን መብት ሲሆን በወራሾች መሀል ብቻ በስጦታ ወይም በሽያጭ ውል ማስተላለፍ የሚቻል ሲሆን ክሊራንስ አይጠየቁም። ይህም የሚጠቅመው ለወራሾች ብቻ ነው።

# 11. ግዙፍነት የሌላቸው ልዩ ልዩ ንብረት ሽያጭ እና ስጦታ ውል

## 11. 1 የአእምሮአዊ ንብረት ሽያጭ ውል

- በህግ አግባብ የተዘጋጀ የውል ሰነድ፣
- እዳና እገዳ ስላለመኖሩ በተቋሙ መረጋገጡን ማጣራት፣
- ከአእምሮዊ ንብረት ጽ/ቤት ወይም ከሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚ/ር የተሰጠ የባለቤትነት ማስረጃ ፣
- የሻጭ 6 ወር ያላለፈበት ያላገባ ማስረጃ ወይም ጋብቻ ካለ የጋብቻ ማስረጃና የተጋቢዎች ስምምነት፣
- የግራ ቀኝ ተዋዋዬችና የሁለት ምስክሮች የታደሰ መታወቂያ።

## 11.2 የአእምሮአዊ ንብረት ስጦታ ውል ስምምነት

- በህግ አግባብ የተዘጋጀ የስጦታ ውል ሰነድ፣
- እዳና እገዳ ስላለመኖሩ በተቋሙ መረጋገጡን ማጣራት፣

- ከአእምሮዊ ንብረት ጽ/ቤት የተሰጠ ማስረጃ ወይም ከሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚ/ር የተሰጠ የባለቤትነት ማስረጃ
- የስጦታ አድራጊው የጋብቻ ማስረጃና/የተጋቢዎች ስምምነት ጋብቻ ከሌለ ይህንኑ የሚያረጋግጥ 6 ወር ያላለፈበት ያላገባ ማስረጃ፣
- የግራ ቀኝ ተዋዋዬችና የሁለት ምስክሮች የታደሰ መታወቂያ

## 11.3 የአእምሮአዊ ንብረት ኪራይ ውል ስምምነት

- በህግ አግባብ የተዘጋጀ የኪራይ ውል ሰነድ፣
- እዳና እገዳ ስላለመኖሩ በተቋሙ መረጋገጡን ማጣራት፣
- ከአእምሮዊ ንብረት ጽ/ቤት የተሰጠ ማስረጃ ወይም ከሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚ/ር የተሰጠ የባለቤትነት ማስረጃ፣
- የአከራይ የጋብቻ ማስረጃ ጋብቻ ከሌለ ይህንኑ የሚያረጋግጥ 6 ወር ያላለፈበት ያላገባ ማስረጃ
- የግራ ቀኝ ተዋዋዬችና የሁለት ምስክሮች የታደሰ መታወቂያ

## ልዩ ልዩ ውሎች

## 12. የብድር ውል ስምምነት በፍ/ብ/ህ/ቁ2471 መሠረት

- በህግ አግባብ የተዘጋጀ የውል ሰነድ፣
- ሁለት የሰው ምስክሮችና የታደሰ መታወቂያቸው፣
- የግራ ቀኝ ተዋዋይ የታደሰ መታወቂያ፣
- የግራ ቀኝ ተዋዋዮች በውክልና ከሆነ የውክልና ሥልጣን
- የተዋዋዩች 6 ወር ያላለፈበት ያላገባ ማስረጃ ወይም ጋብቻ ካለ የተጋቢዎች ስምምነት
- የንግድ ማህበር ከሆነ የመመስረቻ ጽሁፍና መተዳደሪያ ደንብ ወይም ቃለጉባኤ፣
- የስራ አስኪያጁ ውሉን ለመፈራረም የሚያስችል የተረጋገጠ የስልጣን ማስረጃ፣

## 13. ከጋብቻ በፊት የሚደረግ የንብረት ማስመዝገብ ውል ስምምነት የተሻ/ቤ አንቀጽ 42 መሠረት

- በህግ አግባብ የተዘጋጀ የውል ሰነድ፣
- የተዋዋዮች እና የምስክሮች የታደሰ መታወቂያ፣
- የግራ ቀኙ 6 ወር ያላለፈበት ያላገባ ማስረጃ፣

- የንብረት ባለቤትነት ማስረጃ እንደአስፈላጊነቱ

## 14. የቅጥር ውል ስምምነት በዓዋጅ ቁጥር377/96 አንቀጽ 4 መሠረት

- በህግ አግባብ የተዘጋጀ የውል ሰነድ፣
- ሁለት የሰው ምስክሮች፣
- የግራ ቀኝ ተዋዋይና፣ የምስክሮች የታደሰ መታወቂያ፣
- የሙያ ፈቃድ እንደአስፈላጊነቱና እንደሙያው አይነት፣
- ድርጅት ከሆነ የቀጣሪ ሕጋዊ የታደሰ ንግድ ፈቃድ፣
- የንግድ ማህበር ከሆነ የመመስረቻ ጽሁፍና መተዳደሪያ ደንብ ወይም ቃለጉባኤ።

## 15. የመያዣ ውል ስምምነት በፍ/ብ/ህ/ቁ2825 እና 3041 መሠረት

- በህግ አግባብ የተዘጋጀ የመያዣ ውል ስምምነት ሰነድ፣
- እዳና እገዳ ስላለመኖሩ በተቋሙ መረጋገጡን ማጣራት፣
- ሁለት የሰው ምስክሮች፣
- የግራ ቀኝ ተዋዋይና፣ የሁለት ምስክሮች የታደሰ መታወቂያ፣
- የግራ ቀኝ ተዋዋዮች በውክልና ከሆነ የውክልና ሥልጣን፣
- የጋብቻ ወይም ያላገባ ማስረጃ፣
- በመያዣነት የቀረበው ንብረት ማስረጃ ሊብሬ ወይም የባለቤትነት ካርታ፣
- የንግድ ማህበር ከሆነ የመመስረቻ ጽሁፍና መተዳደሪያ ደንብ ወይም ቃለጉባኤ።

## 16. ዳረጐት ውል ስምምነት በፍ/ብ/ህ/ቁ1962 መሠረት

- ትርጉም የዳረጐት ውል ስምምነት የሚፈፀመው በባለ ገንዘቡ እና በተደራጊው ወይም በባለዕዳው እና በተደራጊው ወይም በሶስትዩሽ ሲሆን
  - በህግ አግባብ የተዘጋጀ የዳረጎት የውል ስምምነት፣
  - ዋና የብድር ውል ስምምነት፣
  - ሁለት የሰው ምስክሮች፣
  - የግራ ቀኝ ተዋዋይና፣ የምስክሮች የታደሰ መታወቂያ፣
  - የግራ ቀኝ ተዋዋዮች በውክልና ከሆነ የውክልና ሥልጣን፣
  - በመያዣነት የቀረበው ንብረት የባለቤትነት ማስረጃ ሊብሬ ወይም የባለቤትነት ካርታ፣

- የንግድ ማህበር ከሆነ የመመስረቻና መተዳደሪያ ደንብ እና ዋና ንግድ ምዝገባ
- እዳና እገዳ ስላለመኖሩ በተቋሙ የተረጋገጠ መሆኑ፣
- የዳረጎት ውል ፈፃሚ ባንኮች ሲሆኑ ደብዳቤ።

## 17. የአላባ ጥቅም ውል ስምምነት በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1309/1723 መሠረት

- በህግ አግባብ የተዘጋጀ የአላባ ውል ሰነድ፣
- የባለቤትነት ማረጋገጫ /የቤት ካርታ፣ ሊብሬ/፣
- እዳና እገዳ ባለመኖሩ ከተቋሙ የተረጋገጠ መግለጫ
- የታደሰ የመታወቂያ ሰነድ የአላባ ሰጪና ተቀባይ ወይም ህጋዊ ወኪል፣ምስክሮች፣
- የጋብቻ ወይም 6 ወር ያላለፈበት ያላገባ ማስረጃ፣
- ጋብቻ ካለ የተጋቢዎች ስምምነት።

## 18. ውል ስለማሻሻል

- በህግ አግባብ የተዘጋጀ የማሻሻያ ውል ሰነድ፣
- ቀደም ሲል የተመዘገበው የሚሻሻለው የውል ሰነድ፣
- የግራ ቀኝ ተዋዋይ ወገኖች በውክልና የሚቀርቡ ከሆነ በህግ አግባብ የተሰጠ የውክልና ሰነድ፣
- የግራ ቀኝ ተዋዋይ ወገኖችና የምስክሮች የታደሰ መታወቅያ።

## 19. የውለታን የማስቀረት ስምምነት በፍ/ብ/ህ/ቁ 1819 መሠረት

- ውሉ ቀሪ የሚሆንበት በህግ አግባብ የተዘጋጀ ሰነድ፣
- ቀደም ሲል የተመዘገበው የውል ሰነድ
- የግራ ቀኝ ተዋዋይ ወገኖች በውክልና የሚቀርቡ ከሆነ ከህግ ወይም ከውል የመነጨ ሥልጣን
- የግራ ቀኝ ተዋዋይ ወገኖችና የምስክሮች የታደሰ መታወቂያ፣

የንግድ ማህበር ከሆነ የመመስረቻ ጽሁፍ፣መተዳደሪያ ደንብና ቃለ ጉባዔ

## 20. ሕጋዊ የሰውነት መብት ያላቸውን ማህበራት ስለማቋቋም በንግድ ህግ ቁ313 እና 517 መሠረት

- በህግ አግባብ የተዘጋጀ የመመስረቻና የመተዳደሪያ ደንብ ከ4 ኮፒ ያላነሰ፣
- የስም ስያሜውን የሚያሳይ ማስረጃ ከንግድ ሚ/ር/ ቢሮ የተሰጠ ማስረጃ፣
- በስብሰባው ላይ የተገኙ የአባላት የታደሰ መታወቂያ፣
- በሰነዱ ላይ በአይነት የሚገባ መዋጮ ካለ የንብረቱ ባለቤትነት ማረጋገጫ ሰነድ፣
- ያገባ ከሆነ የጋብቻ ማስረጃ እና የተጋቢዎች ፈቃድ ስምምነት ካለገባ ያላገባ ማስረጃ፣
- ፈራሚዎች በውክልና ከሆነ የውክልና ሥልጣን፣
- ለአካለ መጠን ያልደረሰ አባል ተመዝግቦ የሚገኝ ከሆነ የልደት ሰርተፍኬት ወይም የፍርድ ቤት የሞግዚትነት ማስረጃ ማቅረብ አለበት። የወላጆች የጋራ ፈቃድ ወይም የውክልና ስልጣን፣
- ማህበሩ ባንክና ኢንሹራንስ ወይም ሌላ የገንዘብ ተቋማት ዘርፍ ከሆነ ከኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ በሸኝ ደብዳቤ የተላከና የመመስረቻ ጽሁፍና መተዳደሪያ ደንብ ረቂቅ መቅረብ ይኖርበታል።

  - **አብሮ የመስራት ውል እየተባሉ የሚመጡ ውሎች የህግ መሰረት የሌላቸው በመሆኑ አሰራሩ በንግድ ህጉ መሰረት ከተጠቀሱት የንግድ ማህበራት በአንዱ መነሻ ሊስተናገዱ ይችላሉ..**

- የኩባንያ ወይም የማህበር ስራ አስኪያጅ የሚንቀሳቀስ /የማይንቀሳቀስ ንብረት ለመግዛት/ ለመሸጥ ወይም ለመከራየት ሲመጣ መመስረቻ ጽሁፍ ላይ የስራ አስኪያጁን ስልጣን በተመለከተ በንግድ ህጉና በዚህ መመስረቻ ጽሁፍ የሚሸፈን ይሆናል፣ በሚል የተመለከተ ከሆነ የስራ አስኪያጁ ስልጣን ከንግድ ህጉና በማህበሩ መመስረቻ ጽሁፍ አንፃር መታየት አለበት። ነገር ግን የመመስረቻ ጽሁፍ ላይ የመሸጥና የማከራየት ስልጣናትና ተግባራት ይኖሩታል በሚል በግልጽ ከተመለከተ በዚሁ ማስተናገድ ይቻላል። የስራ አስኪያጁ ተግባራት በንግድ ህጉ ወይም በመመስረቻ ጽሁፍ የመሸጥና የማከራየት ስልጣን እንዳለው በግልጽ ካልተመለከተ ሊስተናገድ አይችልም።
- የኩባንያ ንብረት የሆነ የንግድ ድርጅት ቤት በሚሸጥበት ወቅት የጋብቻ ማስረጃ አይጠየቅም
- ከሃምሳ በላይ አባላት ያላቸው አክስዩን ማህበሮች ለቃለ ጉባኤ የውጭ አገልግሎት በሚፈልጉበት ወቅት

- ❖ ስብሰባው በህግ አግባብ መጠራቱን የሚገልጽ ማስረጃ ከአጀንዳዎቹ ጋር፤
- ❖ በህግ አግባብ የተዘጋጀ ድራፍት የቃለ ጉባኤ ሰነድ፤ሰነዱ ሊይዛቸው የሚገቡ የማህበሩ ሙሉ ስም፤ስብሰባው የተደረገበት ቦታ፤ስብሰባው የተደረገበት ቀን፤በስብሰባው ላይ የተገኙ አባላት በሙሉ፤የስብሰባው አጀንዳዎች፤ውሳኔው የተፃፈበት ወይም የውሳኔው ይዘት፤ የአባላት ጠቅላላ ስምና የፊርማ ቦታ ይኖረዋል።
- ❖ ይህንን ቃለ ጉባኤ ከጽ/ቤታችን በሚላከው ታዛቢ ባለሙያ ፊት ከተፈረመ በኋላ በጉባኤ ምክርቤት አባላትና በቦርድ አባላት በሚቀርብ በፈረሙ አባላት ይውጣልን የቃለጉባኤ ሰነድ አማካይነት ቀደም ሲል የቀረበው የአቴንዳንስ ሽት ተያይዞ ሰነዱ ከህግና ከሞራል ተመርምሮ የተሟላ ከሆነ ወጪ የሚሆን ይሆናል።

  - ማንኛውም የባንክ፤የኢንሹራንስና የገንዘብ ተቋማት መመስረቻ፤መተዳደሪያና ቃለጉባኤዎች የብሄራዊ ባንክ በሰነዶቹ ላይ ማህተም በማድረግ በሸኝ ደብዳቤ ለጽ/ቤቱ መላክ አለባቸው።

20.1 የውጭ አገር ዜጐች ወደነባር አክሲዮን ሲገቡ/አዲስ ሲመሰርቱ

- የንግድ ሚ/ር ደብዳቤ፣
- የሸማቾች ጥበቃና ንግድ ውድድር ደብዳቤ፣
- በኢንቨስትመንት አዋጁ መሰረት ሊከፈል የሚገባ ጥሬ ገንዘብ መከፈሉን ማረጋገጥ፣

20.2 የበጎ አድራጐት ድርጅቶች፣ ህብረት ስራ ማህበራት፣ እድሮች ሽያጭ ኪራይ እና ግዥ ለመፈፀም ሲመጡ

- በህግ አግባብ የተዘጋጀ ውል፣
- የታደሰ ምዝገባ ፍቃድ፣
- የፀደቀ መተዳደሪያ፣
- በሚመለከተው አካል የአመራሮችን ማንነት የሚገልጽ እና ለመግዛት/ለመሸጥ /ለማከራየት የተፈቀደላቸው መሆኑን የሚያሳይ ደብዳቤ፣
- በውክልና ከሆነ የውክልና ስልጣን፣
- የምክስሮች መታወቂያ።

## 21. የእሽሙር ማህበር በንግድ ህጉ ቁጥር 271 መሠረት

- የተዋዋይ ወገኖች የተናጠል/ የግላቸው ዋና የንግድ ምዝገባ
- ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ከሆነ የመመስረቻ ጽሁፍና የመተዳደሪያ ደንብ
- ሁለት ምስክሮች
- የተዋዋይ ወገኖችና የምስክሮች የታደሰ መታወቂያ

## 22. የንግድ ማህበራት የማሻሻያ ቃለ ጉባኤ የንግድ ህግ ቁጥር 411 መሠረት

- በህግ አግባብ የተዘጋጀ ቃለ ጉባኤ ከ3 ኮፒ ያላነሰ
- ተያያዥነት ያላቸው ሰነዶች እንዳስፈላጊነቱ
- የስም ስያሜ ለውጥ ሲኖር የስም ስያሜውን የሚያሳይ ማስረጃ ከንግድ ሚ/ር/ ቢሮ የተሰጠ ማስረጃ፣ከገቢዎች ክሊራንስ፣እዳና እገዳ ማጣራት
- ዋና የንግድ ምዝገባ ሰርተፍኬት
- በስብሰባው ላይ የተገኙ የአባላት የታደሰ መታወቂያ
- በማሻሻያ ቃለ ጉባኤው ላይ በአይነት የሚገባ መዋጮ ካለ በአይነት የተደረገው መዋጮ ከአዲስ አበባ ክልል ውጭ የሚገኝ ከሆነ ንብረቱ ከሚገኝበት ክልል ንብረቱ ከዚህ ቀደም እዳና እገዳ የሌለበትና ህጋዊ ይዞታ መሆኑን በማረጋገጥ በመዋጮ ቢተላለፍ የማይቃወም መሆኑን የሚገልጽ በጽ/ቤቱ አድራሻ የተጻፈ ደብዳቤ
- በቃለ ጉባኤው ውስጥ አክሲዮኑን በሽያጭ ወይም በስጦታ የማስተላለፍ አጀንዳ ካለበት ከገቢዎች ክሊራንስና እዳና እገዳ መጣራት አለበት።
- ያገባ ከሆነ የጋብቻ ማስረጃ እና የፈቃድ ስምምነት ካለገባ ያላገባ ማስረጃ
- ፈራሚዎች በውክልና ከሆነ የውክልና ሥልጣን

## 23. የንግድ ማህበራት ውህደት በንግድ ህግ ቁጥር 549 መሰረት

- በህግ አግባብ የተዘጋጀ የተናጠል ቃለ ጉባኤ ለያንዳንዳቸው ከ3 ኮፒ ያላነሰ
- ውህደት ፈፃሚዎች የጋራ ቃለ ጉባኤ ከ3 ኮፒ ያላነሰ
- ከንግድ ውድድርና ሸማቾች ጥበቃ ኤጀንሲ ውህደቱን የሚፈቅድ ደብዳቤ
- በየግል ክሊራንስ ከገቢዎች
- የተሻሻለ መተዳዳሪያና መመስረቻ ጽሁፍ

- ተያያዥነት ያላቸው ሰነዶች እንዳስፈላጊነቱ
- የስም ስያሜ ለውጥ ካለ እንደአስፈላጊነቱ
- ዋና የንግድ ምዝገባ ሰርተፍኬት
- በስብሰባው ላይ የተገኙ የአባላት የታደሰ መታወቂያ
- ፈራሚዎች በውክልና ከሆነ የውክልና ሥልጣን
- እዳና እገዳ ነፃ ስለመሆኑ

## 24. የንግድ ማህበራት ከአንድ አይነት ወደ ሌላ አይነት አቋም ሲለወጥ በንግድ ህግ ቁጥር 545 እና 547 መሰረት

- ወደ ሌላ አይነት ማህበር እንዲለውጥ የተስማሙበት ቃለጉባኤ
- የተሻሻለ መተዳዳሪያና መመስረቻ ጽሁፍ
- ተያያዥነት ያላቸው ሰነዶች እንዳስፈላጊነቱ
- እዳና እገዳ ማጣራት
- የስም ስያሜ እንዳስፈላጊነቱ እና የስም ለውጥ ክሊራንስ
- ዋና የንግድ ምዝገባ ሰርተፍኬት
- በስብሰባው ላይ የተገኙ የአባላት የታደሰ መታወቂያ
- ፈራሚዎች በውክልና ከሆነ የውክልና ሥልጣን

## 25. ተቋቁሞ የነ33በረን የንግድ ማህበር ስለማፍረስ በንግድ ህግ ቁጥር 217፣495 እና 542 መሰረት

- በህግ አግባብ የተዘጋጀ ቃለ ጉባኤ ከ3 ኮፒ ያላነሰ
- ተያያዥነት ያለው ቃለ ጉባኤ እንደአስፈላጊነቱ
- መተዳዳሪያና መመስረቻ ጽሁፍ
- እዳና እገዳ ማጣራት
- ዋና የንግድ ምዝገባ ሰርተፍኬት
- የፈራሚዎች የታደሰ መታወቂያዎች
- ፈራሚዎች በውክልና ከሆነ የውክልና ሥልጣን

## 26. የንግድ ፈቃድ በአንድ ሰው ስም የሚወጣበት ስምምነት ውል በዓዋጅ ቁጥር 686/02 መሠረት

- በህግ አግባብ የተዘጋጀ የውል ሰነድ
- ሁለት የሰው ምስክሮች
- የግራ ቀኝ ተዋዋይና፣ የምስክሮች የታደሰ መታወቂያ
- የግራ ቀኝ ተዋዋዮች በውክልና ከሆነ የውክልና ሥልጣን
- የፍርድ ቤት ውሳኔ ወይም የወራሽነት ማስረጃ

## 27. ለትርፍ ያልተቋቋመ ማህበራት በዓዋጅ ቁጥር 621/2001 አንቀጽ 64 መሰረት

- በህግ አግባብ የተዘጋጀ የመተዳደሪያ ደንብ ከ4 ኮፒ ያላነሰ
- የስም ስያሜውን የሚያሳይ ማስረጃ ከሚመለከተው አካል
- የፈራሚዎች የታደሰ መታወቂያ
- የዓይነት መዋጮ ካለ ማረጋገጫ
- ፈራሚዎች በውክልና ከሆነ የውክልና ሥልጣን

## 28. ለትርፍ ያልተቋቋመ ማህበራት ማሻሻያ ቃለ ጉበኤ በዓዋጅ ቁጥር 621/2001 አንቀጽ 73 እና በዓዋጅ ቁጥር 334/95 አንቀጽ 5 (1)መሰረት

- በህግ አግባብ የተዘጋጀ የቃለ ጉባኤ ሰነድ ከ4 ኮፒ ያላነሰ
- የማህበሩ የታደሰ ሠርተፍኬት
- ማህበሩ በጽ/ቤቱ ያልተመዘገበ ከሆነ የቦርድ አባላትን ስም ዝርዝር እና ኃላፊነት የሚገልጽ ደብዳቤ ከሚመለከተው አካል መቅረብ አለበት
- የፈራሚዎች የታደሰ መታወቂያ
- የአይነት መዋጮ ካለ ማረጋገጫ
- ፈራሚዎች በውክልና ከሆነ የውክልና ሥልጣን

## ለጽ/ቤቱ ተቀባይነት ያላቸውን መታወቂያዎች

- ከዚህ በታች የተዘረዘሩ መታወቂያዎች ሲቀርቡ የታደሰ፣ ፎቶ ግራፍ የተለጠፈበት፣ማህተም በአግባቡ ያረፈባቸው፣ ስርዝ ድልዝ የሌለባቸው፣ መታወቂያውን የሰጠው ኃላፊ ፊርማ፣ የስምና የኃላፊነት ቲተር በትክክል ያረፈባቸው መሆን አለበት።

  - የቀበሌ የነዋሪነት መታወቂያ፣
  - የትውልደ ኢትዮጵያዊ መታወቂያ
  - የመንግስት መስሪያ ቤቶች ሠራተኛነት መታወቂያ፣
  - የመንግስት ልማት ድርጅቶች ሠራተኛነት መታወቂያ፣
  - መንጃ ፈቃድ፣
  - ፓስፖርት፣
  - የኤንባሲ መታወቂያ
  - የAU/UN መታወቂያ
  - የጠበቃ ፈቃድ፣
  - የውጭ ጉዳይ ሚ/ር ለዲፕሎማቶች የሚሰጥ መታወቂያ
  - የመንግስት ሠራተኞች ጡረታ መታወቂያ፣
  - ሊሴ ፓሴ (የይለፍ) መታወቂያ ጊዜው ያላለፈበትና የታደሰ መሆን አለበት፣
  - የመንግስት ዩኒቨርስቲዎች የቀን ተማሪ መታወቂያ፣
  - የሙያ ሥራ ፈቃድ መታወቂያ
  - የማሪታይም መታወቅያ

# ክፍል ሁለት

## የትኩረት ነጥቦች

- ከፖሊስ ጣቢያ አገልግሎት ፈልገው የሚመጡ ተጠርጣሪዎች ከጣቢያው የአጀበው የፖሊስ ባልደረባ ስም ደብዳቤ ይዘው መምጣት ይጠበቅባቸዋል።
- ለሚመለከተው ተብሎ ወይም በተገልጋዩ ስም ተጽፎ የሚመጣን ክሊራንስ ከዋናው ጋር በማመሰክርና የተመሳከረውን ኮፒ በማያያዝ አገልግሎት መስጠት ይቻላል
- ልዩ ልዩ የሰውነት አካላት ስምምነቶችን ለምሳሌ የኩላሊት፣ ልገሳን በተመለከተ በቃለ መሃላ የሚሸፈን ሆኖ ቃለመሃላውን በሚያደርጉበት ወቅት በሃኪሞች ቦርድ የተረጋገጠ ማስረጃ፣ የለጋሽ የጤና ብቃት ማረጋገጫ ፣የለጋሽ የጋብቻ ወይም ያላገባ ማስረጃ፣ የሰጪና የተቀባይ የገቢ መጠን በቃለመሃላ የተረጋገጠ፣ ለጋሽ ያላገባ ከሆነ የቅርብ ቤተሰብ ፈቃደኝነትን በማያያዝ ወደፊት የህግ ማእቀፍ እስከሚዘጋጅለት ድረስ በጽ/ቤቱ አሰራር በዚህ መስፈርት የሚስተናገዱ ይሆናል።
- መስማት የተሳናቸውና በምልክት ቋንቋ የሚግባቡ ሰዎች ተገልጋይ ሆነው ሲቀርቡ መስማት ከተሳናቸው ማህበር አስተርጓሚ ሰው በደብዳቤ የተመደበላቸው መሆኑን ማረጋገጥ፣
- የውጭ አገር ዜጎች ለመፈረም ይዘውት የሚመጡትን ሰነድ ከመፈረማቸው በፊት ለመረዳት የማይችሉ ከሆነ ከኤንባሲዎቻቸ የአስተርጓሚነት ደብዳቤ ይዘው መምጣት ይጠበቅባቸዋል።
- ማናቸውም ሰነድ ወደ ጽ/ቤቱ ሲቀርብ በዕለቱ መቅረብ አለበት
- የክልል ጠበቃ ከሆነ እዳና እገዳ አይጣራም።

# ክፍል ሶስት

## የፈፃሚዎች ዋና ዋና የስራ ድርሻ

## 3.1. ስምሪት

- ባለሰነዶች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው ሰነዱን ይዘው መቅረባቸውን ማረጋገጥ፣
- ለሚመለከተው ኦፊሰር መምራት ወይም የወረፋ ማስጠበቂያ ማሽን የሚሰጠውን ወረቀት መስጠት፣
- መረጃ መያዝ ፣ መረጃ መስጠት
- ባለጉዳዬች ይዘውት የሚመጡትን የሰነድ ይዘት አለመመርመር

## 3.2. የእገዳ፣ የፊርማ ናሙና እና ፈቃድ ምዝገባ ማረጋገጫ ባለሙያ

- ከፍ/ቤት የሚተላለፉ የእግድና የእግድ ማስነሻ ትዕዛዞች ይመዘግባል፣ ማስረጃ ይሰጣል፣
- አግባብ ያላቸው በመሥሪያ ቤቱ የተፈቀደላቸው አካላት /ባለሥልጣናት/ እና የኃይማኖት መሪዎች የፊርማ ናሙና ያስቀምጣል፣ ሲነሱ ይመዘግባል፣
- የጠበቆች ፈቃድ፣ እገዳ እደሳና ስረዛ ይመዘግባል፣
- አግባብነት ካላቸዉ የትርጉም ጽ/ቤቶች የሚመጡ የፊርማ ናሙናዎችና ፈቃዶች ይመዘግባል፣ ሲነሱ ይመዘግባል፣
- ዶክመንቶችን በአግባቡና በጥንቃቄ ይይዛል፣
- ከእገዳ አጣሪዎችም ሆነ ከሌሎች ሰነድ አጣሪዎች የሚቀርቡለትን የማብራሪያ ጥያቄዎች ተገቢውን መልስና ማብራሪያ ይሰጣል፣

### የንግድ ማህበሮች አበዳሪ ሆነው ሲቀርቡ

- የንግድ ማህበር  ከሆነ የመመስረቻ ጽሁፍና መተዳደሪያ ደንብ ወይም ቃለጉባኤ፣
- ስራ አስኪያጁ  ውሉን ለመፈራረም የሚያስችል የተረጋገጠ የስልጣን ማስረጃ፣
- የታደሰ ዋና ምዝገባ ኮፒ
- የመጨረሻ የኦዲት ሪፖርት የተጣራ ትርፍ የሚያሳይ
- ለመንግስት አስፈላጊ ግብር የተከፈለበት የሚያሳይ ክሊራንስ
- የሚያበድሩት ገንዘብ ከተጣራ ትርፍ በላይ አለመሆኑን ማረጋገጥ
- የምስክሮች መታወቂያ ኮፒ
- በውክልና ከሆነ የውክልና  ስልጣን

- **መዝጋቢው የማጣራት ሥራ መሥራት ዋና ተግባሩ ባይሆንም እንደአስፈላጊው ሊሰሩ ይችላል**

## 3.3. የዕዳና እገዳ አጣሪ ባለሙያ የሥ ራ ድርሻ

- የሚንቀሳቀሱና የማይንቀሳቀሱ ንብረቶች በሽያጭ ወይም በስጦታ ወደ ሶስተኛ ወገን ከመተላለፋቸው በፊት አለመታገዳቸው ማጣራት
- በኢ.ፌዲሪ የፍትህ ሚኒስቴር የተሰጡ የጥብቅና ፈቃድ መታደሳቸውን ማጣራት
- የተለያዩ የመንግስት እና የመንግስት የልማት ድርጅቶች ባለስልጣናት ሥራ አስኪያጆችና እንዲሁም የኃይማኖት መሪዎች የፊርማ ናሙና ያጣራል
- አግባብነት ካላቸዉ የትርጉም ጽ/ቤቶች የሚመጡ የፊርማ ናሙናዎችና ፈቃዶች ያጣራል
- **ባለጉዳዬች ይዘውት የሚመጡትን የሰነድ ይዘት ተያያዥ ሰነዶችን አለመመርመር**

## 3.4 የባለሙያ /የኦፊሰር የሥ ራ ድርሻ

- ማናቸውም ወደ ባለሙያው ሊረጋገጥና ሊመዘገብ የቀረበ ሰነድ ከሥምሪት አሰራሩን ጠብቆ የተመራ መሆኑን የማረጋገጥ
- ሰነዱ ሊይዘው የሚገባ ይዘት(ስም ከነአያት፣ ዜግነት፣አድራሻ )በሙሉ አካቶ መያዙን ማረጋገጥ፣ የሰነዱ ይዘት ለህግና ለሞራል ተቃራኒ አለመሆኑን ማረጋገጥ
- የፈራሚ/ዎች በህግ መሰረት ችሎታ ያለው/ያላቸው መሆኑን የማረጋገጥ
- ሊረጋገጥና ሊመዘገብ የቀረበ ሰነድ በውክልና ከሆነ የውክልና ሥልጣን ማስረጃ
- በሰነዱ ላይ ተለይተው የተጠቀሱ ንብረቶችና መብቶች ካሉ የባለመብቱ ስለመሆናቸዉ ማስረጃ መቅረባቸውን ማረጋገጥ፣
- ወደ ሶስተኛ ወገን የሚተላለፉ ንብረቶችን ከዕዳና ዕግድ ነጻ ስለመሆናቸው በዕዳና ዕገዳ አጣሪው የተጣሩ መሆኑን የማረጋገጥ።

## 3.5 የሰነድ አረጋጋጭ ባለሙያ የሥራ ድርሻ

- ሰነዱ በከፍተኛ ባለሙያ /ኦፊሰር/ ታይቶ መመራቱንና የቀረቡለትን ኮፒ ሰነዶች ተመሳሳይ መሆናቸውን የማረጋገጥ
- እንዲያያዙ የታዘዙት ሰነዶች ዋና/ኦርጅናል/ ከኮፒያቸው ጋር መቅረባቸውን፣
- ለጽ/ቤቱ በአድራሻ የተፃፈ ሰነድ ዋናዉ መቅረቡን፣
- ፈራሚው/ዎች ሰነዱን ለመፈረም ችሎታ ያላው/ቸው መሆኑን ፣
- አግባብነት ያለው መታወቂያ መያዙ/ዛቸውን፣

- ፈራሚው/ዎች ይዘውት ከቀረቡት መታወቂያ ጋር ተመሳሳይ መሆናቸውን፡-
  - ስም/ስማቸው
  - ፎቶግራፍ/ቸው ማረጋገጥ፣
- ፈራሚው/ዎችን ፊርማውን/ቸውን ማስፈረምና ስም/ስማቸውን እንዲፅፉ ማድረግ፣
- በውክልና ወይም በድርጅት ስም የሚፈርም/ሙ ከሆነ "ስለ" የመጀመሪያ ወካይ/ዬች ወይም ስለድርጅቱ ብሎ/ለው ፊርመው ስማቸውን መፃፋቸው፡-
- በጣት የሚፈርሙ ከሆነ በመርገጫ ቀለም የ ጣት ምልክታቸው በሰነዱ መጨረሻ ላይ እንዲያስቀምጡ በማድረግ በጣት ምልክቱ ላይ ስማቸው በሚነበብ መልኩ መፃፍ አለበት፡-
- መስማት የተሳናቸው ከሆኑ መስማት ከተሳናቸው ማኅበር በድጋፍ ደብዳቤ የተላከ አስተርጓሚ መቅረቡን ፣ በትክክል መተርጐሙን አረጋግጦ ከሰነዱ በስተጀርባ መፈረሙን ፣የተረጓሚውን መታወቂያ ማያያዝ፣
- የተፃፈውን የማይረዳ የውጭ አገር ዜጋ ከሆነ ከኤምባሲው የተፃፈ የአስተርጓሚ ማስረጃ ይዞ መቅረቡን ማረጋገጥ፣
  - የአስተርጓሚው መታወቂያ እንዲያያዝ ማድረግ፣ በትክክል ከሰነዱ በስተጀርባ መተርጐሙን ማስፈረም፣
- የማስረጃዎችን እና የመታወቂያዎችን ኮፒ ከዋናው ጋር በማመሳከር ፣ መፈረም፣ ስም፣ ቀን መፃፍ ለእያንዳንዱ የተያያዘ ሰነድ ቁጥር መስጠት፣ ማያያዝ፡ በቀሪው ሰነድ ላይ "በሰነዱ ላይ ስማቸው፣ ዜግነታቸዉና አድራሻቸው የተጠቀሱ ሰዎች መታወቂያቸዉን አሳይተው ኦፊሰሩ በዝርዝር የመራቸው ሰነዶች ተያይዘው በፊቴ ቀርበው ፈርመዋል ". ብሎ መፃፍ፣
- አረጋጋጩ ከኦፊሰሩ የተመራለትን ሰነድ ዳግም ከህግና ከሞራል አንጻር የመመልከት ወይም የመመርመር ብሎም ሰነዱ እንዲስተካከል በማለት ለባለጉዳዩ መመለስ አይችልም።

## የማህተም እደላ

- ሰነዱ በሚመለከተው ኦፊሰርና ሰነድ አረጋጋጭ የተጠናቀቀ መሆኑን ማረጋገጥ፣
- ከሰነዱ ጋር ተያያዥ የሆኑ ማስረጃዎች መያያዛቸውን ማረጋገጥ፣
- በሰነዱ ጀርባ ላይ የገንዝብ ማህተም ተደረገበትና ቴምብር የተለጠፈበት መሆኑን ማረጋገጥ፣
- ሰነዱ ሙሉ በሙሉ መጠናቀቁን በማረጋገጥ የጽ/ቤቱ ክብ ማህተም ማድረግና፣
- ሰነዱ በኮምፒተር መመዝገብ።

# Contents

መግቢያ ........ 1
ክፍል አንድ ........ 2
በጽ/ቤቱ የሚሰጡ አገልግሎቶችና የአገልግሎት ቅድመ ሁኔታዎች ........ 2
1. ውክልና ስልጣን መስጫ ሰነድ ........ 2
1.1 ጠቅላላ ውክልና ........ 2
1.2 የአስተዳደር ስራ ........ 2
1.3 ልዩ ውክልና ........ 3
1.4 የቤተሰብ ውክልና ........ 3
1.5 የጠበቃ ውክልና ........ 3
2. የውክልና ሥልጣን መሻሪያ ........ 4
2.1 የውክልና ሥልጣን ስለመተው/ ........ 4
3. በግልጽ የሚደረግ ኑዛዜ/ ........ 4
4. የኑዛዜ መሻሪያ ........ 4
5. የተተረጐሙ ሰነዶችን ማረጋገጥ በአዋጅ 334/95/ አንቀጽ 3 መሰረት ........ 4
6. በሌሎች ሠነድ የማረጋገጥ ሥልጣን በተሠጣቸው አካላት ተረጋግጠው ........ 5
6.1 በውጭ ጉዳይ ተረጋግጠው የቀረቡ ሰነዶችን መመዝገብ ........ 5
6.2 በመከላከያ ሠራዊት የክፍል ሹሞች ተረጋግጠው የቀረቡ ሰነዶችንመመዝገብ ........ 5
6.3 በፌደራል ማረሚያ ቤቶች ተረጋግጠው የቀረቡ ሰነዶችን መመዝገብ ........ 5
7. የሠነድ ቅጂዎችን ከዋናው ጋር ማመሣከር በዓ/ 334/95 አንቀጽ 12መሠረት ........ 6
8. ቃለ መሃላ ሰነድ ........ 6
9. ማረጋገጫ/ ዲክለሬሽን ........ 6
10. ግዙፍነት ያላቸው የሌላቸው ንብረቶች በውል ስለ ማስተላለፍ ........ 6
10.1 .የተንቀሳቃሽ ንብረት ልዩ ልዩ ውሎችበፍ/ብ/ህ/ቁጥር 2266 መሠረት ........ 6
10.1.1 የመኪና ሽያጭ ውል ኮድ 1፣3፣2 ........ 6
10.1.2 የመኪና ሽያጭ ውል ኮድ 5፣11፣8 እና ሌሎች ........ 7
10.1.3 የመኪና ስጦታ ውል ስምምነት ........ 8
10.1.4 የመኪና ድርሻ ስጦታ/ድርሻ ሽያጭ ለማድረግ ለሚመጡ ባለጉዳዮች ........ 8
10.1.5 የኮንስትራክሽን ማሽነሪ ሽያጭ ወይም ስጦታ ውል ........ 8
10.1.6 የተሽከርካሪ ሞተር ሽያጭ ወይም ስጦታ ውል ........ 9

10.1.7 የተለያዩ ተንቀሳቃሽ ማሽሪዎች ሽያጭ ወይም ስጦታ ....9

10.1.8 የተንቀሳቃሽ ንብረት ኪራይ ውል ስምምነት ....10

10.1.9 የመኪና የድርሻ መልቀቅ ውል ስምምነት ኮድ 1፣2፣3....10

10.2 የማይንቀሳቀሱ ንብረቶች ልዩ ልዩ ውሎች በፍ/ብ/ህ/ቁጥር 1723 እና 2875 መሠረት .... 10

10.2.1 የመኖሪያ ቤት ሽያጭ ወይም ስጦታ ውል.... 11

10.2.2 የንግድ ድርጅት ቤት ሽያጭ ወይም ስጦታ ውል .... 11

10.2 3 የንግድ መደብር ሽያጭ ወይም ስጦታ ውል .... 12

10.2.4 የማይንቀሳቀስ ንብረት ውል ስምምነት በፍ/ብ/ህ/ቁጥር 2696 መሰረት.... 12

10.2.5 የማይንቀሳቀስ ንብረት የድርሻ ስጦታ ወይም ሽያጭ ውል ስምምነት በፍ/ብ/ህ/ቁጥር 1260 እና1262 መሠረት .... 14

10.2.6 የኮንዶሚኒየም ቤት ሽያጭ ውል ስምምነት ....14

10.2.7. የማህበራት ቤት ሽያጭ ውል ስምምነት.... 15

10.2.8 የሊዝ መብት ማስተላለፍ ውል ስምምነት .... 15

10.2.9 የድርሻ መልቀቅ ውል ስምምነት በፍ/ብ/ህ/ቁጥር 1262 ....16

11. ግዙፍነት የሌላቸው ልዩ ልዩ ንብረት ሽያጭ እና ስጦታ ውል ....16

11.1 የአእምሮአዊ ንብረት ሽያጭ ውል ....16

11.2 የአእምሮአዊ ንብረት ስጦታ ውል ስምምነት ....16

11.3 የአእምሮአዊ ንብረት ኪራይ ውል ስምምነት ....17

12. የብድር ውል ስምምነት በፍ/ብ/ህ/ቁ2471 መሰረት ....17

13. ከጋብቻ በፊት የሚደረግ የንብረት ማስመዝገብ ውል ስምምነት የተሻ/ቤ አንቀጽ 42 መሰረት ....17

14. የቅጥር ውል ስምምነት በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 4 መሰረት ....18

15. የመያዣ ውል ስምምነት በፍ/ብ/ህ/ቁ2825 እና 3041 መሰረት ....18

16. ዳረጎት ውል ስምምነት በፍ/ብ/ህ/ቁ 1962 መሰረት ....18

17. የአባላት ጥቅም ውል ስምምነት በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1309/1723 መሰረት ....19

18. ውል ስለማሻሻል ....19

19. የውሌታን የማስቀረት ስምምነት በፍ/ብ/ህ/ቁ 1819 መሰረት ....19

20. ሕጋዊ የሰውነት መብት ያላቸውን ማህበራት ስለማቋቋም በንግድ ህግ ቁ313 እና 517 መሰረት....20

21 የእሽሙር ማህበር በንግድ ህጉ ቁጥር 271 መሰረት ....22

22. የንግድ ማህበራት የማሻሻያ ቃለ ጉባኤ የንግድ ህግ ቁጥር 411 መሠረት.... 22

23 የንግድ ማህበራት ውህደት  በንግድ ህግ ቁጥር 549 መሰረት....22

24 የንግድ ማህበራት ከአንድ አይነት ወደ ሌላ አይነት አቋም ሲለወጥ በንግድ ህግ ቁጥር 545 እና 547 መሰረት ....23

25 ተቋቁሞ የነበረን የንግድ ማህበር ስለማፍረስ በንግድ ህግ ቁጥር  217፣495 እና 542 መሰረት ....23

26 የንግድ ፈቃድ በአንድ ሰው ስም የሚወጣበት ስምምነት ውል በዓዋጅ ቁጥር 686/02 መሰረት ....24

27 ለትርፍ ያልተቋቋመ  ማህበራት በዓዋጅ ቁጥር 621/2001 አንቀጽ 64 መሰረት....24

28. ለትርፍ ያልተቋቋመ  ማህበራት ማሻሻያ ቃለ ጉበኤ በዓዋጅ ቁጥር 621/2001 አንቀጽ 73እና  በዓዋጅ ቁጥር 334/95 አንቀጽ 5 (1)መሰረት ....24

ክፍል ሁለት ....26

የትኩረት   ነጥቦች ....26

ክፍል ሶስት ....27

3 የፈፃሚዎች ዋና ዋና  የስራ ድርሻ....27

3.1 ስምሪት ....27

3.2 የእገዳ፣ የፊርማ ናሙና እና ፈቃድ ምዝገባ ማረጋገጫ ባለሙያ ....27

3.3  የዕዳና እገዳ  አጣሪ  ባለሙያ የሥ ራ ድርሻ....28

3.4   የባለሙያ /የኦፊሰር የሥ ራ ድርሻ ....28

3.5   የሰነድ አረጋጋጭ ባለሙያ የሥራ ድርሻ....28